# <u>የፀረ ሙስና ትግሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትንም ቢያካትት?</u>

**ስለሞን ሽፈራው**

09-08-17

አሁን በዚያ ሰሞን “እውነቱን መነጋገር የህልውና ጉዳይ ሆኖ ሲገኝ” በሚል ርዕስ ያዘጋጀሁትን አንድ መጣጥፍ በዋልታ ኢንፎርሜሽን ድረገጽ ላይ አቅርቤ እንደነበር ትዝ ይለኛል። የዚያ ጽሑፌ ማጠንጠኛ የነበረው መሰረተ ሃሳብ ደግሞ ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበት አጠቃላይ ሁኔታ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ተጨባጭ እውነታውን ፊት ለፊት መጋፈጥና አንቅጩን መነጋገር የሚጠይቅ ሆኖ እንደሚሰማኝ ለመግለጽ የሞከርኩበት ነው ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ ያው የብርቱ ስጋት ስሜቴ አሁንም ድረስ እንዳይለየኝና ሌላ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ርዕሰ ጉዳይ አንስቼ ይበጃል የምልውን ሃሳብ ለመሰንዘር እንድሞክር የሚያስገድድ እውነታ መኖሩ አልቀረም።

ስለዚህም ጉዳዩ ደግመን ደጋግነመን እያነሳን እንወያይበት ዘንድ ግድ የሚል የሀገራዊ ህልውና ጉዳይም ጭምር እንደመሆኑ መጠን፤ እነሆ ዛሬም አንቅጩን ተነጋግረን ልንፈታው ስለሚገባ አንገብጋቢ የጋራ ችግራችን የበኩሌን ሃሳብ ለማቅረብ ስል ብዕር ከወረቀት አገናኝቻለሁና በቀጥታ ወደዋናው ነጥብ እንለፍ። እንገዲያውስ ከጽሑፌ ርዕስ መረዳት እንደሚቻለው ሁሉ፤ የሀገራችን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርስቲዎች) ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ የመምጣቱን ያህል፤ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ተግባርና አስተሳሰብ መገለጫ በሆነ የስነምግባር ችግር የተተበተቡ ተደርገው የሚወሰዱትበት አግባብ ነው ያለው።

ለዚህ አስተያየቴ የተሻለ የመረጃ ምንጭ ሊሆነኝ ይችላል የምለውም ደግሞ፤ ጠቅላይ ሚኒስቴር ኃ/ማርያም ደሳለኝ ዓርብ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርበው ያስጸደቁትን የአዲሱን 2010 ዓ.ም መደበኛ በጀት አስመልክተው ባደረጉት ንግግር ላይ፤ የዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አስደንጋጭ ሊባል የሚችል በጀት አጠቃቀም ዙሪያ ሰፊ ምርመራ አካሔዶ ይፋ ስላደረገው ግኝት ጉዳይ አንስተው ያስረዱበት ገለጻ ነው። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴሩ በዚያን ቀኑ የፓርላማ መድረክ ላይ ተገኝተው፤ አብዛኛዎቹ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ስለሚስተዋለው የበጀት ብክነት ስፋትና ጥልቀት ሲናገሩ የተደመጡበትን አግባብ የሰማ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ፤ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ምን ያህል እንደሀገር ሊያስደነግጠን ወደሚገባ አሳሳቢ ደረጃ እንደደረሰ መገንዘቡ አይቀርም የሚል እምነት አለኝ።

ምክንያቱም ደግሞ፤ የተሻለ እውቀትን ከመልካም ስነ ምግባራዊ ቁመና ጋር ያዋሔደ ወጣት ትውልድ በመቅረጽ ረገድ ቁልፉን አዎንታዊ ሚና ይጫወታሉ ብለን ተስፋ የምናደርግባቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎች) በዚህን ያህል መጠን ወደሚገልጽ የዝቅጠት አደጋ ገብተው ከተገኙ፤ ሌላውን የመንግስት ተቋም ስለሚፈታተነው የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር ለመነጋገር ምን ዓይነት የሞራል ብቃት ይኖረናል? የሚያሰኝ ብርቱ ስጋት ሊያጭርብን ይችላልና ነው። ስለዚህም እኔ እንደ አንድ ሀገራችን

ለምታካሄደው የጸረ ሙስና ትግል ድጋፍ ከመስጠት ቦዝኖ እንደማያውቅ ዜጋ፤ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሁለት መሰረታዊ ነጥቦችን አንስቼ የበኩሌን አስተያየት እሰነዝር ዘንድ ተገቢ መስሎ ይሰማኛል።

እናም የመጀመሪያው በዚህ መጣጥፌ ላነሳው የሚገባ ጠቃሚ ጉዳይ ሆኖ የሚሰማኝ ነጥብ፤ በተለይም የኢፌድሪ ጠቅላይ ኦዲተር መስሪያ ቤት የተቋቋመበትን ሕገ ምንታዊ ኃላፊነት ለመወጣት ሲል የሚያሳየውን ያላሰለሰ ጥረት ስለማድንቅ ነው።

እውነቱን እንነጋገር ከተባለ፤ አሁን ሰሞኑን የፌደራሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የተንሰራፋውን የሙስና ተግባር መርምሮ ይፋ ያደረገበት ሪፖርት በራሱ፤ መስሪያ ቤቱን እጅግ የሚያስመሰግነውና ሀገራችን ላሏት በጣት የሚቆጠሩ የዴሞክራሲ ተቋማት ምሳሌ መሆን የሚችል ጭምር ተደርጎ ሊወሰድለት የሚገባ አበረታች ውጤት ይመስለኛል። በዚህ መሰረትም፤ የዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት ይልቁንም ከጥልቅ ተሃድሶው ንቅናቄ በኋላ ሕገ መንስታዊ ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያደርገው ያላሰለሰ ጥረት ስርዓቱን ገዝግዘው ለመጣል ቆርጠው የተነሱት ኪራይ ሰብሳቢ ኃይሎች በተጠና ቅንብር የዘረጉትን ስውር መረብ ለመበጣጠስና ሀገር አቀፋዊ የጸረ ሙስና ትግሉን ይበልጥ ለማፋፋም የሚያስችለንን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ረገድ አስተዋጽኦው ቀላል አይሆንም ብሎ ማጠቃለል ተገቢነት ይኖረዋል።

ጠቅላይ ኦዲተር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጥልቅ ተሃድሶው መድረክ የተለዩ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ተግባርና አስተሳሰብ መገለጫ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ምቹ ቅድመ ሁኔታዎችን ከማሟላት አኳያ ቀላል ግምት የማይሰጠው አበረታች ጥረት እያሳየ የሚገኝበት እንቅስቃሴ ሁሉ፤ የእርምት እርምጃ የመውሰድ ስልጣን ላላቸው የመንግስት አካላት ሁሉ "ሜዳውም ይሄው፤ ፈረሱም ይሄው!" እንደማለት የሚቆጠር ሆኖ ነው ለኔ የሚሰማኝ። አልያም ደግሞ "ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም " የሚለውን አገርኛ ተረት የሚያንላ አንድምታ አዝሏል ብንል እውነታውን በተሻለ መልኩ ሳይገልጸው አይቀርም። ስለሆነም፤ በዚህ ጽሑፌ ላይ የበለጠ ትኩረት ሰጥቼ አሰምርባቸው ዘንድ ግድ የሚሉ ሁለት መሰረታዊ ነጥቦች አሉ ያልኩበት ምክንያትም ወዲህ ነው። ማለትም፤ የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤቱ አበረታች ጥረት ትርጉም ያለው ተጨባጭ ውጤት ሊኖረው እንዲችል ከተፈለገ በኦዲት ምርመራ ሪፖርቱ የበጀት አጠቃቀም ጉድለት የተገኘባቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ባለድርሻ አካላትን በሕግ እንዲጠየቁ የማድረግ ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ ይገባል የሚለው ቁልፍ ነጥብ እንደ ሀገር የተሟላ የጋራ መግባባት የሚጠይቅ ወሳኝ ጉዳይ ነው የሚል ይሆናል ሌላኛው ገዢ ሃሳብ።

ደግነቱ ግን፤ የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ክቡር አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ ባለፈው ዓርብ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ስለጉዳዩ አንስተው ሲናገሩ፤ በተለይም የዋናው ኦዲተር የምርመራ ውጤት ላይ የጎላ የበጀት ጉድለት የተገኘባቸውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎች) በሕግ እንዲጠየቁ የማድረግ እርምጃ መወሰዱ እንደማይቀር ነው የገለጹት። እናም እርሳቸው በዚያ የፓርላማ መድረክ ላይ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ጠንከርና ከረር ያለ የቁርጠኝነት ቃና ባዘለ ድምጽ ለምክር ቤቱ አባላት የሰጡትን ማሳሰቢያ፤ ወደ ተግባር በመተርጎም ረገድ፤ ሕገ መንግስታዊ

ኃላፊነታቸውን መወጣት የሚጠበቅባቸው ባለድርሻ አካላት ሁሉ የጉዳዩን አንገብጋቢነት በቅጡ ተገንዝበው፤ አጥፊዎችን ሕግ ፊት እያቀረቡ ፍትሐዊ ዳኝነት የማሰጠት ስራ ይሰራሉ የሚል ጽኑ እምነት ማሳደሬን ነው በዚህ አጋጣሚ የምገልጽላቸው።

አለበለዚያ ግን፤ እቺው የጋራ ቤታችን ናት የምንላት ምስኪን ሀገር፤ እንብዛም በማያወላዳ ምጣኔ ሀብታዊ አቅሟ እንደምንም ጥርሷን ነክሳ የምትገነባቸው ዩኒቨርሲቲዎቻችን እንዲህ እንደአሁኑ የብልሹ አሰራር መገለጫና የኪራይ ሰብሳቢ ኃይሎች መፈንጫ ተቋማት ወደ መሆን እየተቀየሩ ሲመጡ የሚስተዋሉበት ነባራዊ እውነታ ባለበት ውስጥ እነርሱ አሰልጥነው የሚያስመርቋቸው በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣት ምሁራን ዜጎቻችን "ሙስናን የሚፀየፉ" እንዲሆኑ መጠበቅ ከእባብ እንቁላል የእርግብ ጫጩት ይፈለፈላል ብሎ እንደማመን ያህል ከንቱ ምኞት ይሆናል። ይህን የምለውም ደግሞ አንዳች የጨለምተኝነት መንፈስ ስለተጠናወተኝ አይደለም።

ይልቅስ ግልሰብም ሆነ ህብረተሰብ ያልዘራውን ያጭድ ዘንድ እንደማይቻለው የገሃዱ ዓለም ተጨባጭ እውነታ በዘመናት ሂደት ውስጥ ደጋግሞ ሲያረጋግጥልን የኖረ ነባራዊ ጥሬ ሃቅ ስለሆነ እንጂ። ስለዚህም፤ ለህዳሴው ዘመን ኢትዮጵያውያን ወጣች፤ የላቀ እውቀት መቅሰሚያና ፈርጀ ብዙ ጥበብ ማፍለቂያ እንዲሆኑ ታስቦ የሚገነቡት ከፍተኛ የትምህርት ተቋሚት፤ ወይም ደግሞ ዩኒቨርሲቲዎቻችን፤ ጥቂት ለሀገርና ለወገን ዘላቂ ዕጣፈንታ የሚያስቡበት ህሊና ያልፈጠረባቸው ሙሰኞች እንዳሻቸው ሲፈነጩ የሚስተዋሉባቸው ኪራይ መሰብሰቢያ ይሆኑ ዘንድ አንፈቅድም ባይ ነኝ እኔ በግሌ።

በተለይም ደግሞ የዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት ምርመራ ላይ የተመለከተውን የየዩኒቨርሲቲዎቹ ምሁራዊ የሥነምግባር ንቅዘት በማባባስ የሚታወቁት አብዛኛዎቹ ልሂቃን ዜጎቻችን፤ እቺን ሀገር ከሚፈታተኗት የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ እንዲሁም የማህበራዊ ችግር መገለጫ ድክመቶች እነርሱ "ነፃ" ስለመሆናቸው የሚገልጹበትን አጉል መመፃደቅና መንግስትን ብቻ ተጠያቂ አድርገው ለማቅረብ የሚሞክሩበትን አግባብ ስናስታውስ፤ ጉዳዩ እጅግ በጣም አስተዛዛቢም ጭምር ሆኖ ሊታየን ይችላል። ምክንያቱም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱን አጠቃላይ ቁመና ለስማቸው በሚመጥን አስተዳደራዊ ብቃትና የመልካም ሥነ ምግባር እሴት የሚገልጽ እንዲሆን የማድረግ ሙያዊ ኃላፊነት መወጣት የሚጠበቅባቸው የየዩንቨርሲቲዎቹ ማህበረሰብ ልሂቃን በ"እኔ የለሁበትም" ዓይነት ጲላጦሳዊ መገበዝ እጃቸውን እየታጠቡ ከደሙ ንፁህ ነን ለማለት ሲቃጣቸው የሚስተዋሉበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለምና ነው።

ስለሆነም በአብዛኛዎቹ የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎች) ውስጥ ክፉኛ እየተባባሰ እንደመጣ የሚነገርለትን ለቦታው የማይመጥን የሞራል ኪሳራና የሥነ-ምግባር ዝቅጠት በቅጡ የመፈተሽ ጥረት ማድረግ ካለብን፤ አሁን ላይ የዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት ባካሄደው የኦዲት ምርመራ ውጤት አማካኝነት ይፋ የሆነውን ግብዓት እንደመልካም አጋጣሚ ከመጠቀም የሚሻል አማራጭ መፍትሄ ሊኖር እንደማይችል ለመረዳት የተለየ እውቀት አይጠይቅም። የጉዳዩን አሳሳቢነት በሚመለከት ዛሬ እንኳን ትርጉም ያለው የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ሳንችል ቀርተን፤ ዩኒቨርሲቲዎቻችን የሙሰኞች መፈንጫ ሆነው ቢቀጥሉ ግን፤ ታሪክ ይቅር የማይለው ስህተት እንደመፈጸም ይቆጠራል የሚል እምነት ነው ያለኝ እኔ።

ስለዚህ በዋናው ኦዲተር ወቅታዊ ሪፖርት የተገለጸውን የበጀት ብክነት ያስከተለ ምዝበራ ስለመፈጸማቸው የሚያመለክት መረጃና ማስረጃ የቀረበባቸውን የየዩንቨርሲቲዎቹ ባለድርሻ አካላት ሕግ ፊት እየቀረቡ ለጥፋታቸው የሚመጥን ቅጣት እንዲሰጣቸው የማድረግ ጉዳይ ይዋል ይደር የሚባል አይደለም የሚለውን ነጥብ በድጋሚ ልናሰምርበት ይገባል። ይልቁንም ደግሞ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የፌደራሉ መንግስትና እንዲሁም የክልላዊ መስተዳደሮች የሥራ ኃላፊዎች ይሄን መረጃ ተከትለው በመንቀሳቀስ የምዝበራው መሪ ተዋንያን ለህግ ለህግ የማቅረብ ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት እንደሚጠበቅባቸው ይታመናል። እናም ያን ማድረግ አለማድረግ ትርጉም ያለው የተጠያቂነት አሰራር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለምልዓተ ህዝቡ ማረጋገጥም ጭምር ተደርጎ ሊወሰድ ስለሚችል፤ መሪዎቻችን ከታሪክ ተወቃሽነት የሚያድናቸውን የእርምት እርምጃ ወስደው የመጪው ትውልድ ባለውለታ ይሆኑ ዘንድ ነው የምመኘው። በመጨረሻ የፌደራል ጠቅላይ ኦዲተር መስሪያ ቤት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱን አስተዳደራዊ ንቅዘት ይፋ በማውጣት ረገድ ላሳየው ጥረት ያለኝን አድናቆት ለመግለጽ እወዳለሁ።